## በሎስአንጀለስ ለታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ገንዘብ ለማሰባሰብ በተካሄደ የምሽት ዝግጅት ከ 1.7 ሚሊዮን ብር  በላይ ድጋፍ ለማድረግ ቃል ተገባ::

በሎስአንጀለስና አካባቢው ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለሕዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ ለማሰባሰብ ያዘጋጁት የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት መስከረም 13/2004 በሎስአንጀለስ ሒልተን ሆቴል ተካሂዷል:: በምሽቱ ቁጥራቸው 500 የሚሆን ተሳታፊዎች ተገኝተዋል::

በሎስአንጀለስ የሕዳሴ ግድብ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ አዳል ኢሳው ባደረጉት ንግግር አገራችንን የማሳደግና ከድህነት የማላቀቅ ጉዳይ የጋራ ጉዳይ መሆኑን አመልክተዋል:: በተለይ የታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ጉዳይ ብዙ የሚያጠያይቅ መሆን እንደሌለበት ፣ ግድቡ ካለን የፖለቲካ ልዩነት በላይ የሆነና ሕዝባችንን ከድህነት ለማለቀቅ እየተካሄደ ያለ ግንባታ በመሆኑ ሳንለያይ በአንድነት ልንደግፈው የሚገባ መሆኑን ገልፀዋል፡

የዕለቱ የክብር እንግዳ አምባሳደር ዘሪሁን ረታ በሎስአንጀለስ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ቆንሱል ጄኔራል ባደረጉት ንግግር በአገራችን እየታየ ያለው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ላስከተለውና በከፍተኛ መጠን እያደገ ላለው የሀይል ፍላጎት አስተማማኝ ምላሽ የሚሰጥ የሀይል አቅርቦት እንዲኖር መንግስት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ቀርፆ ሲንቀሳቀስ መቆየቱን በእዚህም  የሀይል ማመንጨት አቅማችንን 2000 ሜጋ ዋታ ማድረስ መቻሉን አስረድተዋል:: በቅርቡ ግንባታው የተጀመረው ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ለፈጣን የአገራችን ልማት አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ሀይል ምንጭ በመሆን ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ለተያያዝነው ትግል ቁልፍ ድርሻ የሚኖረው መሆኑን አመልክተዋል:: የአገራችን ህዝቦች ከውጭ የሚመጣ ወራሪ ጠላትን በጋራ በመመከት ነፃነታቸውን ጠብቀው እንደኖሩ ሁሉ ግንባር ቀደም ጠላታቸው የሆነውንና የአገራቸውን ስም ባጎደፈው ድህነት ላይ በአንድነት እየተረባረቡ የሚገኙ መሆኑን ጠቅሰው ለሕዳሴው ግድብ እውን መሆን ከፍተኛ ድጋፍ እየሰጡ የሚገኙትም ግድቡ ድህነትን በመዋጋት ረገድ ያለውን ፋይዳ በመገንዘባቸውና የፀና እምነት በመያዛቸው መሆኑን ገልጸዋል :: አያይዘውም በውጭ የሚኖረው ማህበረሰብ አገራችንን በድህነትና  ኋላቀርነት  የሚያሳውቃት ገፅታ እንዲለወጥና ከተመፅዋችነት እንድትላቀቅ በሙሉ ልቡና አቅሙ በድህነት ላይ እየተካሄደ ያለውን ትግል መቀላቀል

እንደሚኖርበት አመልክተው ለታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ የበኩሉን ድርሻ እንዲያበረክትና በእዚህ ታሪካዊ ግድብ ላይ አሻራውን እንዲያኖሩ ጥሪ አድርገዋል፡፡

በምሽቱ ከ 100 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ወይም ከ 1.7 ሚሊዮን ብር በላይ ቦንድ ለመግዛትና የገንዘብ ስጦታ ለማድረግ ቃል የተገባ ሲሆን በርካታ ተሳታፊዎች ደግሞ የቃል መግቢያ ቅፅ በመውሰድ የሚያደርጉትን ድጋፍ መጠን የሚያሳውቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከእዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ምክንያቶች በዝግጅቱ ላይ መገኘት ያልቻሉ የማህበረሰቡ አባላት ለግድቡ ድጋፍ እንደሚያደርጉ በተለያዩ መንገዶች የገለፁ በመሆኑ የሚገኘው ድጋፍ ከፍ እንደሚል ይጠበቃል፡፡